የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ...፯
አዲስ አበባ ታህሳስ ፮ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. …7
ADDIS ABABA 15th December, 2025

ማውጫ

ደንብ ቁጥር.....፭፻፹፩/፪ሺ፲፰

የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፬/፩ሺ፱፻፺፮ ለማሻሻል የወጣ ደንብ.....

.....ገጽ ፲፱፬፲፫

Content

Regulation No…..581/2025

Council of Ministers Regulation to Amendment for Immigration Regulation No. 114/2004.....

.....Page 19413

ደንብ ቁጥር ፭፻፹፩/፪ሺ፲፰

የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ

የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፬/፩ሺ፱፻፺፮ (እንደተሻሻለ) እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፬/፩ሺ፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፫ ንዑስ (፩) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፭፻፹፩/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ማሻሻያ

የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፬/፩ሺ፱፻፺፮ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

REGULATION No. 581/2025

COUNCIL OF MINISTERS IMMIGRATION (AMENDMENT) REGULATION

WHEREAS, it is necessary to amend Council of Ministers Immigration Regulation No. 114/2004 (as amended);

NOW THEREFORE, the Council of Ministers has issued this regulation in accordance with Article 23 Sub-Article(1) of Immigration Proclamation No. 354/2003 (as amended)

1. Short Title

This regulation may be cited as the "Council of Ministers Immigration Amendment Regulation No…581/2025".

2. Amendment

Immigration Council of Ministers Regulation No. 114/2004 (as amended) is hereby amended as follows:

፩. የደንቡ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣(ለ) እና (ሠ) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ሀ)፣(ለ) እና (ሠ) ተተክተዋል።

"ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት.....አምስት ዓመት፤
ለ) ሰርቪስ ፓስፖርት.....አምስት ዓመት፤
ሠ) የውጭ አገር ሰው ፓስፖርት....ሶስት ዓመት፤"

፪. ከደንቡ አንቀጽ ፳ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፳፩፣ ፳፪፣ ፳፫ እና ፳፬ ተጨምረው ነባሮቹ አንቀፆች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፳፩ - ፵፭ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

"፳፩. <u>ወርቃማ ቪዛ</u>

፩/ ወርቃማ ቪዛ ከአስር ሚሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስት ለሚያደርግ የውጭ ሀገር ሰው የሚሰጥ የቪዛ አይነት ነው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ከአምስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስት ለሚያደርግ እና ለአገሪቱ ኢኮሚያዊ እድገት ፋይዳ ባለው እንደ የስራ ዕድል ፈጠራ ወይም ቴክኖሎጂ አመንጪነት ለሚሳተፍ የውጭ ሀገር ሰው በልዩ ሁኔታ ወርቃማ ቪዛ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) ዝርዝር አፈፃፀም በመመሪያ ይወሰናል።

፬/ ወርቃማ ቪዛ በየአስር ዓመቱ የሚታደስ የብዙ ጊዜ የመመላለሻ ቪዛ ነው።

፳፪. <u>ቤት ለሚገዛ የውጭ ዜጋ የሚሰጥ ቪዛ</u>

፩. ቤት ለሚገዛ የውጭ ዜጋ የሚሰጥ ቪዛ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ ለሆነ የውጭ አገር ሰው ይሰጣል፡፡

1. Paragraph (a), (b) and (e) of Sub-article (1) of Article 11 of the Regulation has been deleted and replaced by the following new paragraph (a), (b) and (e).

"a) Diplomatic Passport.....5 years;
b) Service Passport .....5 years;
C) Alien Passport ..... 3 years;"

2. After Article 20 of the regulation, the following new Articles 21, 22, 23 and 24 have been added, and the existing Articles renumbered as Articles 25 – 45, respectively:

21. <u>Golden Visa</u>

1 / Golden visa is a type of visa issued to a foreigner who invests over ten million dollars.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a Foreign National who invests over five million dollars and participates in an activity that is favourable to the economic development of the country, such as job creation or technology transfer may be granted a golden visa under special circumstances .

3/ The detail implementation of Sub Article (1) and (2) of this Article shall be determined by the directive.

4/ Golden visa is a multiple-entry visa that is renewable every ten years.

22. <u>Visa for a foreigner buying a house</u>

1. Visa shall be issued to a foreigner who is the owner or possessor of immovable property in Ethiopia in accordance with the relevant laws.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት የሚሰጥ ቪዛ በየአምስት ዓመቱ የሚታደስ የብዙ ጊዜ የመመላለሻ ቪዛ ነው፡፡

፳፫. <u>የተግባራዊ ልምምድ ቪዛ</u>

የተግባራዊ ልምምድ ቪዛ ለጊዜያዊ የስራ ልምምድ ለሚመጣ የውጭ ሀገር ሰው የሚሰጥ የቪዛ አይነት ነው ፡፡

፳፬. <u>የመውጫ ቪዛ</u>

የመውጫ ቪዛ ከሀገር ለሚወጣ የውጭ ሀገር ሰው የሚሰጥ የቪዛ አይነት ነው፡፡

፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

2/ a visa issued as per Sub-article (1) of this Article shall be a multiple-entry visa that is renewable every Five years.

23. <u>Internship Visa</u>

Internship Visa is issued to a foreign national who comes to the country for a temporary internship.

24. <u>Exit visa</u>

Exit visa is a type of visa issued to a foreigner leaving the country.

3. <u>Effective Date</u>

This regulation shall come into force from the date of its publication in the Federal Gazette.

አዲስ አበባ ቀን ታህሳስ ፮/፪ሺ፲፰ ዓ.ም

አብይ አህመድ(ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

Done at Addis Ababa on date of December 15/2025.

Abiy Ahmed (Dr)
Prime Minister of the Federeal Democratic Republic of Ethiopia